ለወደፊት የምታወግዟቸው ጉዳዮችና አድልዎ ይከሰታል!' ሶሐቦችም 'የአላህ መልክተኛ ሆይ! ምን ያዙናል?' አሉ። እርሳቸውም 'በናንተ ላይ ያለባችሁን ግዴታ ትወጣላችሁ። ለናንተ ያላችሁን ሐቅ ደግሞ ከአላህ ትጠይቃላችሁ።' አሉ።

ከኢብኑ መስዑድ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም
በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል፦ "ለወደፊት የምታወግዟቸው ጉዳዮችና አድልዎ ይከሰታል!' ሶሐቦችም 'የአላህ መልክተኛ
ሆይ! ምን ያዙናል?' አሉ። እርሳቸውም 'በናንተ ላይ ያለባችሁን ግዴታ ትወጣላችሁ። ለናንተ ያላችሁን ሐቅ ደግሞ ከአላህ
ትጠይቃላችሁ።' አሉ።"
[ሶሒሕ ነው።] [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) የሙስሊሞችን ገንዘብና ሌሎችንም አለማዊ ጉዳዮች በማዳላት ሙስሊሞች እርሱ ላይ ያላቸውን መብት በመከልከል እንደፈለጉ የሚያወጡ መሪዎች በሙስሊሞች ላይ እንደሚሾሙ ተናገሩ። በነርሱ ላይም የሚወገዙ ሃይማኖታዊ ጉዳዮች እንደሚኖራቸው ተናገሩ። ሶሐቦችም (ረዲየሏሁ ዐንሁም) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና በዚህ ሁኔታ ላይ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ጠየቁ። ነቢዩም (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) በገንዘብ ጉዳይ ብቻቸውን መጠቀማቸው በናንተ ላይ ለነርሱ ልታሟሉ ግዴታ የሆነባችሁን ከመስማትና ከመታዘዝ እንዳይገታችሁ። ይልቁንም ታግሳችሁ መስማትና መታዘዝ ላይ አደራችሁን። በትእዛዞቻቸውም አትቃረኗቸው (አትከራከሯቸው)። እንዲያስተካክላቸው፣ ክፋታቸውንና ግፋቸውን እንዲከላከልላችሁ ለናንተ ያላችሁንም ሐቅ ከአላህ ጠይቁ!

http://www.sunnah.global/hadeeth/am/show/3156